# የ ትውልድ

የ«የ ትውልድ ተቋም» ልሳን

የ ትውልድ ቅጽ 3 ቁጥር 6 ነሐሴ ፳፮ ቀን ፪ ሺህ ፭ ዓ.ም.

## <u>“ደማችሁ ደማችን”</u>

*(ኢሕአፓ የታወጀበትን 41ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*






የዛሬ ሶስት ዓመት ተኩል የተመሠረተችና ህልውናዋን በይፋ ሳይገልጽ ሲታገል የቆየው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከዛሬ ሶስት [illegible] በፊት በተደረገው ኮንፈረ ንሱ [illegible] የተቀረጸን የሠፊው ሕዝብ ትግል በይፋ በመውጣት ለማፋፋም፣ ለማቀናበርና ለመምራት ወስኗል::

ከ1964 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ በህቡዕ ሲንቀሳቀስ የነበረው ኢ.ሕ.አ.ፓ ነሐሴ 21 ቀን 1967 ዓ.ም. ባወጣው “ዴሞክራሲያ” ልሳኑ ቅጽ 2 ቁጥር 13 እራሱን ለሕዝብ ይፋ ያደረገበት 41ኛ ዓመት። በቀጣይ ቀናት ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) ራሱን አወጀ። ኢ.ሕ.አ.ፓ በዚህ ቀን የፓርቲ ፕሮግራሙን ያወጣውና የተሰራጨው በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግሪኛ፣ በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛና በአረብኛ ቋንቋዎች ነበር።

ለኢ.ሕ.አ.ፓ ቤተሰቦችና ደጋፊዎች እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሞላ እንኳን አደረሳችሁ መልዕክታችን ከ«ያ ትውልድ ተቋም» ይድረሳችሁ።

ኢ.ሕ.አ.ፓ “ፋኖ ተሰማራ” ብሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጭቆና ቀንበር ሊያላቅቅ “ብረት አንሳሁ፤ ለትግል ተነሳሁ” ብሎ እነሆ ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያቀና ቀዳሚ ፓርቲ ነበር። የኢ.ሕ.አ.ፓ መሥራች ልጆች ከነበራቸው ዘመናዊ ትምህርት ደረጃ በአጠቃላይ ለግል ሕይወታቸውና ኑሯቸው ከማንም የማያንሱ ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ ደረጃም በወቅቱ በገቢያቸው ዳጎስ ካሉ ቤተሰቦች የፈለቁ በርካታ ናቸው። መደባቸውን ለሚወዱት ሕዝባቸውና ሀገራቸው የለገሱ በርካታ ናቸው። ያስተማራቸውን ሕዝብ ሥቃዩን ሊቀርፉለት “የትግሉ ነው ሕይወቴ” ብለው ግምባር ቀደም ፋና ወጊ ሆነውለታል። ሕዝባቸውን ሊያድኑ የዜግነት መብቱን “የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ” መፈክራቸው ዛሬም ይስተጋባላቸዋል። ሀገር ለሕዝብ ብለው “መሬት ለአራሹ” ጬኸታቸው ዛሬም አታጋይነቱ የነበራቸውን አርቆ አሳቢነት ያጎላዋል። “ህዘንሽ ህዘኔ” ብለው ስለ ሀገር ጮኸዋል። “ብሶትሽ ብሶቴ” ብለው ስለ ሴቶች መብት “ያገር ያለህ” ብለዋል። የኢ.ሕ.አ.ፓ ታሪክ ሲነሳ መፈክሮቹ፣ ትግሉ፣ ጀግንነቱ፣ ቆራጥነቱ፣ የተከፈለው መስዋእትነት፣ ተጋድሎው፣ በተለያየ መልኩ ቃላት ቢወረወሩ የሚያደምቀው ነው። ለተፈለገው ድል ባይበቃም ታሪኩ እጅግ አስተማሪ ነውና ቢፃፍ ያኮራል፣ ቢነገር ይደመጣል፣ ቢተረክ ዓይን ዕምባ ይቋጥራል፣ ቢዘመር ስሜትን ይመስጣል።

ኢ.ሕ.አ.ፓ ሐምሌ 11 ቀን 1966 ዓ.ም. “አደባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ” በሚል የ“ዴሞክራሲያ” የመጀመሪያ ዕትሙ ቅጽ 1 ቁጥር 1 የየካቲት 66ን ሕዝባዊ አብዮት አስታኮ ሲያስነብብ እንዲህ ነበር ያለው።


ዴሞክራሲያ

ቁ.1
11-11-66

አደባባይ ሰው ቢያርሱ በአረም ይ...

በየካቲት ወር የፈነዳው የህዝቡ ትግል እነሆ እንደቀጠለ ነው። ትግሉ በኢትዮጵያ ፖለቲካ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል ለማለት ይቻላል። በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ሕዝቡ ለመጀመሪያ ጊዜ በፖለቲካ መድረክ ብቅ ብሏል። ይህ እንቅስቃሴ ታላቅ የሚያሰኙትና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከዚህ በፊት ከካሄዷቸው የፖለቲካ ትግሎች ሁሉ ልዩ የሚያደርጉት:—

አንደኛ:— በትግሉ የተካፈለው ሕዝብ ብዛትና ስፋት

ሁለት :— ትግሉ በገጠር መደብ ... ይዞ መውጣት

ሶስት :— የቀረቡት ጥያቄዎች ዓይነትና ትግሉ ያስያዛቸው ለውጦች ናቸው።

እነሆ ዛሬም ከ41 ዓመት በኋላ በሀገራችን ኢትዮጵያ እየተፋፋመ ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በየቦታው ከተነሳሳው ፀረ-ወያኔ ተጋድሎና ከአካተተው የህብረተሰብ ተሳትፎ አኳያ ሲታይ ተመሳሳይነት ሲኖረው፤ ሊካድ የማይችለው በወያኔ አገዛዝ የተረጨው የ25 ዓመት ዘረኝነት የትግሉን አሰላለፍ ላይ በመጠኑም ቢሆን ነጸብራቁን አሳይቷል። አሁን ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ትርጉሙን እንዲያገኝ ከተፈለገ አሁንም የኦሮሞ ልጆች፣ የአማራው ልጆች፣ የትግራይ ልጆች፣ የጉራጌ ልጆች፣ የደቡብ ልጆች፣ የጋምቤላ ልጆች፣ የኦጋዴን ልጆች፣ እስላሙና ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ "ደማችሁ ደማችን" ብለን እንደትላንቱ፣ እንደጥንቱ ኢሕአፓ ስለ ሀገር፣ ስለ ሕዝብ በጋራ መደጋገፍ ይኖርብናል። የሁሉም ጥያቄ አንድ ነውና። የዜግነት መብት፣ የሕዝብ መንግስት ጥያቄ፣ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች መፈታት ጥያቄ፣ የረሃብና ድህነት የኑሮ ጥያቄ ወዘተ. በአንድ ሀገር ልጆች ለዘመናት መልስ ያላገኘ አንድ ወጥ ጥያቄ። እጅ ለእጅ እንድንያያዝና እናት ሀገራችንን ከበታኞች እናድናት ዘንዳ የኢሕአፓ ታሪክ አስተማሪነቱን ለማስገንዘብ ዛሬ ይፋ የሆነበትን 41ኛ ዓመት ስናስታውስ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ማያያዙን ፈለግን። ያኔ የኢሕአፓ ልጆች ዘርና ሃይማኖት ሳይገድባቸው ተቃቅፈው ዘምረው፣ ተያይዘው ተሰልፈው፣ በአንድነት ታግለው በፋሺስት ጥይት ተቃቅፈው ወድቀዋል። ዛሬም "የኦሮሞ ደም ደማችን ነው" ብለው የወያኔን ዘረኝነት የበጠሱት አማሮች፤ ትግሉ ለሀገር ስለ ሀገር መሆኑን ግንዛቤ ሊወሰድ ያስፈልጋል።

ኢሕአፓ ገና ያልተፃፈባቸው በርካታ "ዴሞክራሲያ" ዕትሞች አሉት። ከምሥረታው ጀምሮ እራሱን ይፋ እስካወጀበት የዛሬ 41 ዓመት ድረስ በቅጽ 1, 25 ዕትሞችና አራት ልዩ ዕትሞች በማስነበብ በቅጽ 2, 12 ዕትሞች በጥቅሉ 41 ዕትሞች በማስነበብ ቅጽ 2 ቁጥር 13 ሲደርስ እራሱን ይፋ ያወጣበት ታሪካዊዋ ዴሞክራሲያ ከጅምሩ እንዳስቀመጥነው ተነባለች።

ውድ አንባብያንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! «ያ ትውልድ ተቋም» በአለፉት አራት ዓመት ጉዟችን የያ ትውልድን ታሪክ በተለይ የኢሕአፓን የተገኙትን መረጃዎች በማሰባሰብና በድረ ገፃችን (www.yatewlid.com, www.yatewlid.org) በማካተት ለተጠቃሚዎች በቀላሉ የሚያገኙበትን ለማመቻቸት ሞክረናል። ወደፊትም ይቀጥላል።

ኢ.ሕአፓ ይፋ የሆነበትን 41ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ይህንን በዓል ኢ.ሕአፓን እጅጉን ውበት ለሰጠችውና፣ ኢ.ሕአፓ ማነው? የሚለውን ለአስተዋወቀችው፣ ኢ.ሕአፓ "ቤት ለእምቦሳ" ብሎ በሕዝብ ሊታቀፍ ኃይልና ጉልበት ለሆነችው፣ ኢ.ሕአፓ ሲነሳ ሁሌም ለምትጠቀሰው "ዴሞክራሲያ" ዕትሙ መታሰቢያ አድርገናል።

*" "ዴሞክራሲያ" በኢ.ሕአፓ ታትማ የምትወጣ የፓርቲው ልሳን ናት። "ዴሞክራሲያ" ኢ.ሕአፓ ራሱን በፓርቲነት ይፋ ከማድረጉ ዓመት በፊት ቀደም ብላ መውጣት ጀምራለች። የ"ዴሞክራሲያ" የመጀመሪያ ዕትም ቅጽ 1 ቁጥር 1 ነሐሴ 11 ቀን 1966 ዓ.ም. "አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" በሚል ርዕስ ወጥታ ለሕዝብ ተሠራጭታ ለንባብ በቅታለች።*

*""ዴሞክራሲያ" በውብ ቋንቋና አገላለጽ፣ በአማርኛ ውበቷ፣ የቀረበውን ርዕስ ይዛ አጀማመሯና አወራረዷ አጨራረሷ፣ ሊተላለፍ የሚፈለገውን መልዕክት ሲያሻት ቀለል ባለ አገላለጽ ሲያስፈልግም ተመራምረን እንደርስበት ዘንድ ያላት እምቅ ኃይል፣ የአፃፃፍና የቋንቋ ሀብቷ እጅግ ማራኪና ተናፋቂ አጓጊ አደረጋት። "ዴሞክራሲያ" ኢ.ሕአፓ ማነው? ለሚለው ማንነትን ማሳያ፣ "ዴሞክራሲያ" የሀገር ልሳን፣ የህዝብ ሀብት፣ የወጣቶች አሳዳጊ፣ የማትናቅ የትግል፣ የድርጅት ሀብት መሆኗ ጠላት ሳይቀር መሰከረላት። "ዴሞክራሲያ" ኢ.ሕአፓን አሳደገች፣ ወጣት አደራጀች፣ አባቶችን ናፈቀች፣ ተዓምር ሊፈጥር የሚችል አንድ ትውልድ አሰባሰበች። "ዴሞክራሲያ" ለአባላቱ መኩሪያ መከታ፣ ጋሻ ጃግሬ እንኳንም ኢ.ሕአፓ ሆንኩ አሰኘች። በ"ዴሞክራሲያ" ልፋት ለመብትና ነፃነት እስርና ሞትን ያስተናገደ፣ ለሀገርና ሕዝብ ክብር ሞትን የተጋፈጠ ትውልድ አፈራች።*

*""ዴሞክራሲያ" በአንድ ዓመት ወደ 30 ዕትሞች አስነብባለች። በመለጠቅም እስከ 1972 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ በ6 ቅጾች በትንሹ ወደ 87 የሚጠጉ ዕትሞችና በትንሹ 12 ልዩ ዕትሞች አስነብባለች። "ዴሞክራሲያ" በወቅቱ በፓርቲው የሚወሰዱትን የፖለቲካና ኢኮኖሚ አቋም፣ ፖሊሲና ዕቅዶችን እንዲሁም ወቅታዊ ቅስቀሳዎችን ይዛ ወጥታለች። "ዴሞክራሲያ" ፓርቲው ተግባራዊ ሊያደርግ ያቀደውን ቀደም ብላ ታሳውቃለች። ትጠቁማለች። በብሔር ጥያቄ፣ በዴሞክራሲያ ጥያቄ፣ በሶማሊያ ጦርነት እና በሌሎች የፓርቲውን አቋም በግልጽ አስቀምጣለች። መንግስት ያከናወናቸውን ጥፋቶች አጋልጣለች፣ የሚያቅዳቸውንም ቀደም ብላ ታሳውቃለች። መደረግ የሚኖርበትንም ጠቁማ አታግላለች። "ዴሞክራሲያ" በጣፋጭ አንደበቷ፣ በማራኪ ትንተናዋ፣ በውብ ቋንቋዋ ኢ.ሕአፓን አስተዋውቃለች። ኢ.ሕአፓን ከሕዝብ አስተቃቅፋለች። ፋሽስትና ባንዳን አውላላ ሜዳ ላይ አንሳፋለች። ደርግ "ዴሞክራሲያ"ን በዴሞክራሲያ ሳይሆን በጥይት እስከበጣጠሰበት ድረስ የትግሉን መፈክሮች ከፍ አድርጋ ተፋልማለች። በርካታ ጀግኖች አፍርታለች።" ከ ፍፁም ነው እምነቴ መጽሐፍ የተወሰደ።*

የኢ.ሕአፓ ታሪክ ሲነሳ በደም የጨቀየ ታሪካቸውን ለመሸፈን "የትን ለቅሶ መልሶ መላልሶ" እንዲሉ "ተኮሰብን" እንዳልሆነ ዛሬም የ"ዴሞክራሲያ" እትሞቹ በግልጽ መቀመጣቸውን ማሳወቅ ይኖርብናል። ዓይኖች ማየት ካልተሳናቸው፤ ለሕዝብና ሀገር ፓርቲውና ልጆቹ የነበራቸውን ጥልቅ ስሜት ከልሳኑ "ዴሞክራሲያ" ማግኘት ይቻላል።

የኢ.ሕአፓ ታሪክ ያኔ "አናርኪስት" ተብሎ እንደተፈረጀ ሁሉ ዛሬ በዘመነ ወያኔ የሕዝብ ትግል በ"አሸባሪነት" መፈረጁ የአምባገነኖችና የገዳዮች ባህሪ አንድና አንድ መሆኑን መስካሪ ነው። ኢ.ሕአፓ ከምሥረታው ጀምሮ በአሳለፈው የትግል ታሪክ እንኳን በጥሩ ጎኑ በድክመቱም የሚያፍር አይደለም። በሀገሪቷ ቀደምት ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን ከተመክሮና ልምድ ማጣት ሌላም ቢባል የተሠሩ ስህተቶች ዛሬም አስተማሪ ናቸውና ይቀበላቸዋል። እንደ ደርግ ገዳዮች ስህተት አልሰራሁም ብሎ ሲሸፈጥና ያንን ስህተት ለመሸፈን ታሪክን እየበረዙ እንደሚጽፉት አሳፋሪነት ጥንትም ዛሬም አልተጠናወተውም። ኢ.ሕአፓ ታሪኩ

ተጽፎ የማያልቅ ገና ብዙ ጥናትና ምርምር የሚደረግበትን መረጃ ያስቀመጠ ለመሆኑ ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ «ያ ትውልድ ተቋም» በድረ ገፃችን ያሰባሰብነውን የ44 ዓመት ዴሞክራሲያ እትሙን (በትንሹ ወደ 270 ዕትሞች) ማንበብ በቂ ነው። በየጊዜው በተከሰቱ ሀገራዊ ጉዳዮች አቋሙ በግልጽ በራሱ ብዕር በ"ዴሞክራሲያ" ልሳኑ ተከትበዋል።

የኢሕአፓን ልሳን "ዴሞክራሲያ"፣ አንደበቱን ከየቤተ መጽሐፍቱ እየቀዳደዱ ታሪኩን ለማጥፋት ጥረት ማድረጉ አይደለም ጀግንነት። ያኔ "ቀይ ሽብር ይፋፋም!"፣ "አስታጥቁን አታስጨርሱን" እየተባለ የተፎከረበትን ልሳን እየደበቁ አይደለም ከጥፋት መሸሽ። ታሪክ ተመራማሪዎች ከሁሉም አቅጣጫ ጥናታቸውን ያደርጉበት ዘንድ የፃፉትንና የፈረሙበትን ሠነድ ደብዛ በማጥፋት አይደለም መኩራራት። እውነተኛውን መረጃ በማጥፋት ታሪክን ጥላሸት እየቀቡ መፃፍና ማውራት ለተሠራው ግፍ መሸፋፈኛም ይሁን ምላሽ አይሆንም።

በኢሕአፓ ቤተሰቦችና ወገኖችም በኩል የዛሬ 41 ዓመት ዴሞክራሲያ ዕትም ከላይ እንዳየነው ለመነበብ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆን እንረዳለን። ቤት ውስጥ በካርቶን አሽጎ የማስቀመጥ ውጤት የፈጠረው ነው። ዛሬ በአለ የኮምፒዩተር ዲጂታል ሥልጣኔ መረጃዎችን ከማስቀመጥ ይልቅ በኋላ ቀር አያያዝ እንዳይነበቡ ስናደርጋቸው ልናፍር ይገባናል። ኢሕአፓ የሕዝብ ሀብት ነው። ኢሕአፓ ወራሽ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ኢሕአፓ "ፍፁም ነው እምነቴ፤ የትግሉ ነው ሕይወቴ" ብለው ያሸለቡ አባላቱና ወገኖች ቤተሰብ ሀብት ነው። እናማ መረጃዎቹን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ከኢሕአፓ ወገኖች ይጠበቅብናል። ከእኛ የሚጠበቀው በታሪካችን እስካላፈርን ድረስ ታሪካችን አስተማሪ ይሆን ዘንድ ብቅ ማድረግ። በግልም ሆነ በድርጅት ደረጃ ያለንን የፎቶም ሆነ የጽሁፍ መረጃ ወደ ዘመኑ ስልጣኔ ኮምፒዩተር ዳታ ቤዝ በማስገባት ለተጠቃሚና ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስረከብ እንደሚገባን በዚህ አጋጣሚ ልናሳስብ እንወዳለን።

በመጨረሻም ዛሬ ኢትዮጵያ ሀገራችንና ሕዝባችን የህልውናና የማንነት ተጋድሎ ከወያኔ/ኢሕአዴግ ጋር ይዘዋል። ሕዝባዊ ትግሉ ለመብትና ለሕዝብ መንግስት ምሥረታ እንደመሆኑ መጠን መቀናጀትን ይጠይቃል። በምንም መልኩ በወያኔ/ህወሀት የዘር ወጥመድ ሳይካተቱ በአንድነት ይህንን አገዛዝ ለማስወገድና የጥፋት ዘመኑ በነበር ወደ ታሪክ አተላነት ይካተት ዘንድ በአንድነት መጓዝን ይጠይቃል። ከኢሕአፓ የትግል ታሪክ ብዙ ልንማር እንችላለን። በመላ ሀገሪቷ በፓርቲ ደረጃ ዳር እስከዳር በርካታ አባላትን አፍርቶ፣ በርካታ ቤተሰቦችን አቅፎ፣ ዘር፣ ክልልና ሃይማኖት ሳይገድበው እንደ ሕዝባዊነቱ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል አካቶ ከዛሬ ነገ ሀገርና ሕዝብን ነፃ አወጣ የተባለለት ፓርቲና ትግል ታሪክ ሆኖ ቀርቷል። እንኳንስ ተነጣጥለን እየተጓዝን።

ዛሬ በወያኔ ጥይት እየረገፈ ያለው ሕይወት ሀገርንና ሕዝብን ነፃ ማውጣት ይኖርበታል። "ሰው ሊኖር ሰው ሞቷል" ነውና ሀገራችን ኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነቷን ጠብቃ ዴሞክራሲያን መሠረት ያደረገ ሕዝባዊ አንድነት ዕውን ሊሆን የሚችለው የሚፈሰው የንጹሐን ደም "ደማችሁ ደማችን" ብለን የጋራ ጠላት ላይ ትኩረት ሲደረግ መሆኑን ልናሳስብ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ይፋ የወጣበትን 41ኛ ዓመት ስናከብር ለሀገራችንና ለሕዝባችን አንድነትና ደህንነት ያለንን ፍቅር በማስተጋባት ነው። እነሆ ወያኔ ይገድላልና፣ እነሆ ወያኔ ጨካኝ ነውና አንበርክክ። ድል የኢትዮጵያና የሕዝቧ እንደሚሆን አንጠራጠር። ብርሃን ለሀገር ሲፈነጥቅ ጨለማ ወያኔን ይሸፍነዋል። ጉብዝና ሕዝባችንን ሲያጅብ ፍርሃት ወያኔን ውጦታል። ድል ለሀገራችን፣ ድል ለህዝባችን ውድቀት ለወያኔ ጊዜው ቀርቧል። ውድ የኢትዮጵያ ልጆች እየከፈላችሁ ያላችሁት የአካልና የሕይወት መስዋዕትነት ለሀገራቹ ነውና፣ ለሕዝባችሁ ነውና ታሪክ በደማችሁ ይፃፋል። አድኑኝ ላለች እናት ሀገራችሁ ሆ! ብላችሁ መነሳታችሁ አኩሪ ነውና ዞር ብላችሁ እንዳትመለከቱ።

ክብር ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ!!!

«ያ ትውልድ ተቋም»

ዋቢ ማጣቀሻ፡

- ነሲቡ ስብሐት፡ "ፍፁም ነው እምነቴ" ቀይ ሽብር የከፍተኛ 15 እውነተኛ ታሪክ፤ መስከረም 2007 ዓ.ም. ሰሜን አሜሪካ።
- የኢሕአፓ ልሳን ዴሞክራሲያ ዕትሞች፦ ያ ትውልድ ድረ ገጽ (www.yatewlid.com, www.yatewlid.org)

ነሐሴ ፳፮ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ.ም.

(September 1, 2016)

ኢሜል ፦ yatewlid@gmail.com, yatewlid@yahoo.com, yatewlid@hotmail.com